የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ኤምባሲ
አታዋ
**EMBASSY OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**
**OTTAWA**



# የሐዘን መግለጫ

በካናዳ አታዋ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ኤምባሲ ባልደረቦች ሚያዝያ 10 ቀን 2007 ዓ.ም ISIS ብሎ ራሱን የሰየመው አሸባሪ ቡድን በኢትዮጵያዊያን ወገኖቻችን ላይ በሊቢያ የፈፀመውን የግፍ ጭፍጨፋና አረመኔያዊ ድርጊት እንዲሁም በደቡብ አፍሪካ በወገኖቻችን ላይ የተፈፀመ ግድያና ዝርፊያ በፅኑ እያወገዝን፤ የተሠማንን ጥልቅ ሃዘን እንገልፃለን፡፡ ለሟች ቤተሰቦች፣ በካናዳ ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን እንዲሁም ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መፅናናትን እንመኛለን፡፡

ይህንኑ አስመልክቶ አታዋ በሚገኘው የኤምባሲው ጽ/ቤት ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን፣ዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ እንዲሁም ወዳጆቻችን የተሰማቸውን ሀዘን መግለጽ እንዲችሉ ከኤፕሪል 22-24 ቀን 2015 የሚቆይ የሐዘን መግለጫ መዝገብ የተከፈተ መሆኑን እንገልፃለን፡፡ በተጨማሪም **በቶሮንቶ፣ አታዋ፣ ኤድመንተን፣ ቫንኮቨር፣ ካልጋሪና ዊኒፔግ** በተዘጋጀው የህሊና ፀሎትና የሻማ ማብራት ስነስርዓት በመገኘት በዜጎቻችን ላይ የደረሰውን አሰቃቂ ግድያ ለማውገዝ፣ፀረ-ሽብር ትግላችን የበለጠ ለማጠናከር እና ለሟች ቤተሰቦች የሀዘናቸው ተካፋዮች መሆናችንን በጋራ እንድንገልፅ ኤምባሲው በማክበር ጥሪውን ያቀርባል፡፡



**ኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ኤምባሲ**

**አታዋ**

Embassy of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Ottawa

